**ማስታወቂያ**

**ለተከበራችሁ የኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች በሙሉ**

የኢትዮጵያ የንግድ ህግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 ለአክሲዮን ማኀበር መተዳደሪያ ደንብ እውቅና የማይሰጥ በመሆኑና የማኀበሩንና የአስተዳደር አካላትን ተግባራትና ኃላፊነት የሚወስነው መተዳደሪያ ደንብ በሕግ አግባብ ተቀባይነት ስለሌለው የመተዳደሪያ ደንቡን ድንጋጌዎች በመመስረቻ ጽሑፍ ውስጥ ማጠቃለል በማስፈለጉ እንዲሁም ከዚህ ቀደም በማኀበሩ መመስረቻ ጽሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ በየጊዜው የተደረጉ ማሻሻያዎችን በማጠቃለል በንግድ ህጉ አንቀፅ 255 መሰረት የተቀመጡትን መስፈርቶች በሚያሟላ መልኩ የተሻሻለ የመመስረቻ ፅሁፍ ማዘጋጀት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ በኩባንያው የተዘጋጀውን ረቂቅ የተሻሻለ የመመስረቻ ጽሁፍ ከኩባንያው ድረ-ገፅ ላይ የተጫነ መሆኑን እየገለጽን ያላችሁን አስተያቶችም ሆነ ማናቸውንም ግብዓቶች በአካል ለኩባንያው የሕግ አገልግሎት ወይም ለማህበሩ ፀሀፊ እንድትሰጡልን ወይም በኩባንያው የመልእክት ሣጥን ቁጥር 170791 ወይም በኩባንያው የኢሜል አድራሻ info@eliginsurance.com እንድትልኩልን ወይም ህዳር 22 ቀን 2016 ዓ.ም. በሚደረገው የባለአክሲዮኖች ጉባኤ ላይ እንድታቀርቡ በትህትና እንጠይቃለን።

**የኢትዩ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አ.ማ**

**የዳይሬክተሮች ቦርድ**

## ኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር
## የተሻሻለ መመስረቻ ጽሁፍ

### መግቢያ

የኢትዮጵያ የንግድ ህግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 የአክሲዮን ማኅበር መተዳደሪያ ደንብን እውቅና የማይሰጥና፤ አክሲዮን ማኅበሩ ደግሞ የማኅበሩንና የአስተዳደር አካላትን ተግባራትና ኃላፊነት የሚወስን ዝርዝር መተዳደሪያ ደንብ ያለው በመሆኑ እነዚህን የመተዳደሪያ ደንብ ድንጋጌዎች በመመስረቻ ጽሑፍ ውስጥ ማጠቃለል በማስፈለጉ፣

ኩባንያው ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ በተደረጉ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔዎች በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ በየጊዜው የተደረጉ ማሻሻያዎችን እና የተጨመሩ አዳዲስ ድንጋጌዎችን ሁሉ በማጠቃለል በአንድ የመመስረቻ ጽሑፍ ሰነድ ማደራጀት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ የሕግ ማጣቀሻ ድንጋጌዎች፣ ቃላትና ሃረጎች ከአዋጅ ቁጥር 1243/2013 ድንጋጌዎች አንጻር ማስተካከያ ማድረግ በማስፈለጉ፣

የኩባንያው ባለአክሲዮኖች ህዳር 22 ቀን 2016 ዓ.ም ባደረጉት 10ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በመሥራች አባላት የጸደቁትን የማኅበሩ መመሥረቻ ጽሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ድንጋጌዎች በማሻሻልና በመመስረቻ ጽሑፉ ውስጥ በማጠቃለል በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 400 (1) መሰረት ይህን የተሻሻለ የመመስረቻ ጽሁፍ አጽድቋል፡፡

### አንቀፅ አንድ
### የማህበሩ ስም

የማህበሩ ስም “ኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር” ነው፡፡

### አንቀፅ ሁለት
### የማህበሩ ዋና መ/ቤት እና ቅርንጫፎች

1. የማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 2፣ ቤት ቁጥር 659፤ የመልእክት ሳጥን ቁጥር 170791፤የስልክ ቁጥር 251 11 554 9651፤ የፋክስ ቁጥር 251 11 554 9653፤ ኢ.ሜል አድራሻ info@eliginsurance.com፤ ዌብሳይት www.eliginsurance.com ነው፡፡
2. ማህበሩ በኢትዮጵያ በማናቸውም ቦታና እንደ አስፈላጊነቱም ከኢትዮጵያ ውጪ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች እና ወኪል ጽ/ቤቶች ማቋቋም ይችላል፡፡

## አንቀፅ ሶስት
## የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ስም፣ አድራሻ እና ዜግነት

የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ስም ዜግነት እና አድራሻ በአባሪ አንድ ላይ የተመለከተው ነው፡፡

## አንቀፅ አራት
## ማኅበሩ የተሰማራበት የንግድ ሥራ ዓላማ

ማህበሩ የተሰማራበት የንግድ ሥራ ዓላማ እንደሚከተለው ነው፡-

1. በኢትዮጵያ እና ወይም ከኢትዮጵያ ውጭ ማንኛውንም ጠቅላላና ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የመድህን እና የጠለፋ መድን ንግድ ሥራ ማከናወን፤
2. የጠለፋ መድን (Reinsurance) ድርጅቶች ውስጥ አክሲዮን በመያዝ ወይም ካፒታል ኢንቨስት በማድረግ መሳተፍ፤
3. የመድንና የጠለፋ መድን ድርጅቶች ወኪል ሆኖ መሥራት፤
4. ከመድን ንግድ ሥራ ጋር ተመሳሳይነት ያለውን ወይም ከእነዚህ ጋር ተያያዥነት ያለውን የንግድ ሥራ ማከናወን፤
5. በማይንቀሳቀስ ንብረት ዋስትና፣ በግዴታ ሰነዶች፣ በአክሲዮኖች እና በማይንቀሳቀሱ ንብረቶች የንግድ ሥራ ላይ ኢንቨስት ማድረግ፤
6. በመድንና በሌሎች የኢንቨስትመንት የሥራ ዘርፎች የምክር፣ የማኔጅመንት አገልግሎትና አጫጭር ሥልጠናዎችን መስጠት፤
7. በመድን ሥራ ዘርፍ ላይ እውቀትን እና ዘርፉ የደረሰበትን ወቅታዊ እድገት የሚገልጽ የሕትመት ሥራዎችን ማከናወን፤
8. የንብረት አስተዳደር ሥራ መሥራት፤
9. ከመድን ሥራ ጋር ግንኙነት ያላቸውንና ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ለማሳካት የሚያስችሉ እና በሕግ የተፈቀዱ ሌሎች የንግድና የኢንቨስትመንት ሥራዎችን ማከናወን፡፡

## አንቀጽ አምስት
## የማህበሩ አባላት የፈረሙት የአክሲዮን ብዛትና የተከፈለው የገንዘብ መጠን

የማህበሩ የተፈቀደ ዋና ገንዘብ ብር 690,000,000.00 (ስድስት መቶ ዘጠና ሚሊዮን) ነው፡፡ ይኸውም የነጠላ ዋጋቸው ብር 1,000.00 (አንድ ሺህ ብር) በሆኑ 690,000 (ስድስት መቶ ዘጠና ሺህ) ተራ አክሲዮኖች የተከፋፈለ ሲሆን ከዚሁ የተፈቀደ ዋና ገንዘብ ብር 200,000,000.00 (ሁለት መቶ ሚሊዮን) የተከፈለ ነው፡፡ በእያንዳንዱ ባለአክሲዮን የተያዘ የአክሲዮን ብዛትና የተከፈለ የአክሲዮን ዋጋ በአባሪ አንድ ላይ የተመለከተው ነው፡፡

## አንቀፅ ስድስት

## የአክሲዮኖች ዓይነት

የማህበሩ አክሲዮኖች አንዳችም ልዩነት የሌለባቸው፣ የማይከፋፈሉ፤ አንድ ዓይነቶች የሆኑ እና ቅድሚያ መብት የማይሰጡ ናቸው፡፡ እያንዳንዳቸው አክሲዮኖች በባለአክሲዮኑ ስም የተመዘገቡ፣ እኩል ዋጋ ያላቸው እና ተራ አክሲዮኖች ናቸው።

## አንቀፅ ሰባት

## የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ኃላፊነት

በኢትዮጵያ የንግድ ህግ አንቀፅ 295 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የባለአክሲዮኖች ኃላፊነት በማህበሩ ውስጥ ባላቸዉ የአክሲዮን መጠን የተወሰነ ነው፡፡

## አንቀጽ ስምንት

## የባለአክሲዮኖች መብት

እያንዳንዱ ባለአክሲዮን የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡፡

1. በአስቸኳይም ሆነ በመደበኛ ጉባዔዎች ራሱ በአካልም ሆነ በውክልና በመገኘት ሃሣብ የማቅረብ፤ የመቃወም፤ ድምፅ የመስጠት፤
2. የማኅበሩን ጠቅላላ ጉባኤ ዉሣኔ የመጠየቅና የማግኘት፤
3. የአክሲዮን ባለቤትነት የምስክር ወረቀት የማግኘት፤
4. የማኅበሩን የተጣራ ትርፍ እንዲሁም ማኅበሩ ከፈረሰ በሚደረገዉ የሂሣብ ማጣራት ድርሻን የመካፈል፤
5. የመምረጥና መመረጥ፣ የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ እጩ ሆኖ የመቅረብ፤
6. ካፒታል በመጨመሩ ተጨማሪ አክሲዮኖች የሚመደቡ ቢሆን በያዘው አክሲዮን ምጣኔ መሰረት በቀደምትነት ድርሻ የመግዛት፤
7. በማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት በመገኘት የሂሳብ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሳራ መግለጫዎችን፣ ዳይሬክተሮች እና ኦዲተሮች ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀረቡዋቸውን ሪፖርቶች እና የተያዙ የጠቅላላ ጉባኤ ቃለ ጉባዔዎችን የመመርመር ወይም ቅጂዎችን የመውሰድ፤
8. አግባብ ባለው ሕግና በዚህ የተሻሻለ መመሥረቻ ጽሑፍ ለባለአክሲዮኖች የተሰጡ ሌሎች መብቶችን የመጠቀም፡፡

## አንቀፅ ዘጠኝ
## አክሲዮን ስለማስተላለፍ

1. አክሲዮኖችን ያለምንም ገደብ በሽያጭ፣ በስጦታ እና በሌሎች በሕግ በተፈቀዱ መንገዶች ለባለአክሲዮንም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ማስተላለፍ ይቻላል፤
2. በአክሲዮን መዝገብ ያልተመዘገበ የአክሲዮን ዝውውር ዋጋ የለውም፤
3. በአክሲዮን ዝውውር ምክንያት የሚከፈል ግብርና ታክስ ቢኖር እንደሁኔታዉ አክሲዮን አስተላላፊዉ ወይም ተረካቢዉ የመክፈል እና ግብሩ ስለመከፈሉም በፅሑፍ የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸዉ፡፡

## አንቀፅ አስር
## የጋራ ባለቤትነት፤ መያዣ እና አላባ

1. አክሲዮኖችን በጋራ ባለቤትነት መያዝ ይቻላል፡፡ አክሲዮኖችን በጋራ የያዙ ባለአክሲዮኖች ወኪል ይሾማሉ፡፡ የሾሙትን ሰው ስምና አድራሻም በባለአክሲዮኖች መዝገብ ያስመዘግባሉ፡፡ ማህበሩ መጥሪያውን የሚልከው ለዚሁ ለተሾመው የባለአክሲዮኖች ተወካይ ይሆናል፤
2. የጋራ ባለመብቶች ተወካይ ባልተሰየመበት ሁኔታ ለአንድ የጋራ ባለንብረት የተሰጠ ማስታወቂያና ውሳኔ ለሁሉም ባለመብቶች እንደተሰጠ ይቆጠራል፤
3. አክሲዮኑን በመያዣ ወይም በአላባ ያስያዘ ባለአክሲዮን ስሙን፤ አድራሻውን፤ በመያዣ እና በአላባ መብት ያስያዘበትን ምክንያት እና ቀሪ መብቱን በግልጽ ማስፈር አለበት፡፡ ኩባንያው ማስታወቂያና ውሳኔዎችን መላክ በሚኖርበት ጊዜ በውሉ ውስጥ በተለይ ካልተመለከተ በስተቀር ለመያዣ እና ለአላባ መብት ተጠቃሚዎች ይልካል፤
4. አክሲዮን በመያዣ ወይም በአላባ የተሰጠ እንደሆነ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር በማህበሩ ጉባኤዎች ደምጽ የመስጠት መብት የሚኖረው አክሲዮኑን በመያዣ የያዘው ወይም የአላባ ጥቅም ያለው ሰው ነው፤
5. አክሲዮኖችን በጋራ በባለቤትነት ከያዙት ውስጥ አንዱ ቢሞት የሟቹ ድርሻ የሆኑ አክሲዮኖች በሕግ አግባብ ለሟቹ ወራሾች ይተላለፋሉ፡፡

## አንቀፅ አስራ አንድ
## የባለአክሲዮኖች መዝገብ

1. የባለአክሲዮኖችን ዝርዝር የያዘ መዝገብ በማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት ይደራጃል፤ መዝገቡ በሕግና በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ የሚጠየቁትን መረጃዎች ሁሉ የያዘ መሆን አለበት፤

2. ባለአክሲዮኖችና የሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች መዝገቡን ያለአገልግሎት ክፍያ መመልከት ይችላሉ፡፡ ሆኖም ባለአክሲዮን ያልሆነ ሰው መዝገቡን ማየት የሚችለው ለዚሁ ተብሎ ማህበሩ የወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም ነው፡፡

## አንቀጽ አስራ ሁለት
## የአክሲዮን የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

ማህበሩ ለባለአክሲዮኑ የሚሰጠዉ የአክሲዮን ምስክር ወረቀት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀፅ 273 የተቀመጠዉን የይዘት መስፈርቶች የሚያሟላ ይሆናል፡፡ ማህበሩ የመጀመሪያ የአክሲዮን ባለቤትነት የምስክር ወረቀት ያለምንም ክፍያ የሚሰጥ ሲሆን ባወጣው የአክሲዮን የምስክር ወረቀት ላይ ጉዳት ቢደርስ፣ ቢበላሽ፣ ቢጠፋ፣ ወይም ቢሰረቅ የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ተለዋጭ የአክሲዮን የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ የፊተኛው አክሲዮን የምስክር ወረቀት ዋጋ አይኖረውም፡፡

## አንቀጽ አስራ ሦስት
## ሕጋዊ የመጠባበቂያ ገንዘብ

1. ማህበሩ በህግና ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በየዓመቱ ከተጣራ ትርፍ ላይ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ገንዘብ ተቀማጭ ያደርጋል፤
2. የመጠባበቂያ ሂሣቡ ከማህበሩ የተከፈለ ካፒታል እኩል ሲደርስ ከተጣራ ትርፍ በየዓመቱ የሚያዘው የመጠባበቂያ ሂሣብ መጠን ከተቆጣጣሪው ባለሥልጣን በሚሰጥ መመሪያ ይወሰናል፤
3. ከዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም ከኦዲተር ሃሳብ የቀረበለት እንደሆነ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው ተጨማሪ ወይም አማራጭ የመጠባበቂያ ገንዘብ እንዲኖር መወሰን ይችላል፡፡

## አንቀጽ አስራ አራት
## የትርፍ ክፍፍል

1. የማህበሩ ትርፍ ለባለአክሲዮኖች የሚከፋፈለው የሚከተሉት ወጭዎች ከተቀነሱ በኋላ በመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት ነው፡-
    1.1. ጠቅላላ የአስተዳደር ወጪዎች፤
    1.2. ግብር፤ ቀረጥና ሌሎች ግዴታዎች፤
    1.3. ህጋዊ ተቀማጭ ገንዘብ/መጠባበቂያ
    1.4. በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ወይም በባለአክሲዮኖች ጉባኤ በሚወሰነው መሰረት የሚፈቀዱ ሌሎች መጠባበቂያ ሂሳቦች፤
    1.5. ያለፉት አመታት ኪሳራዎች፤

1.6. ለዳይሬክተሮች ቦርድና ለሌሎችም አካላት የተፈቀዱ ወጪዎችና ክፍያዎች፡

1.7. አግባብነት ባላቸው የአገሪቱ ሕጎች መሰረት ተቀናሽ መሆን ያለባቸው ሂሣቦች ናቸው፡፡

2. የባለአክሲዮኖች የትርፍ መጠን የሚሰላው በማህበሩ ውስጥ ባላቸው የተከፈለ ካፒታል መጠንና የተከፈለ ካፒታሉ በበጀት ዓመቱ የተከፈለበትን ጊዜ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

## አንቀጽ አስራ አምስት

## የማህበሩ የአስተዳደር አካላት

ማህበሩ የሚከተሉት የአስተዳደር አካላት ይኖሩታል፡፡

1. የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ፤
2. የዳይሬክተሮች ቦርድ፤
3. ዋና ሥራ አስፈፃሚ፤
4. የማህበሩ ፀሐፊ፤ እና
5. ኦዲተር ናቸው፡፡

## አንቀጽ አሥራ ስድስት

## የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ

1. **ጠቅላላ ደንቦች**

1.1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የማህበሩ የበላይ አካል ነው፡፡ ጠቅላላ ጉባዔ መደበኛ ወይም አስቸኳይ ሊሆን ይችላል፡፡ ሁሉም ባለአክሲዮኖች ከተስማሙ በሁለቱም ዓይነት ጉባኤዎች በአካል በመገኘት ስብሰባ ማድረግ ሳያስፈልግ ለውሳኔ በቀረበ ጉዳይ ላይ ባለአክሲዮኖች ሀሳባቸዉን በፅሑፍ ወይም በአሌክትሮኒክ ዘዴ እንዲገልጹ በማድረግ ማስወሰን ይቻላል፤

1.2. አግባብነት ባለዉ ሕግ የተቀመጠዉ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ለማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ የሚያደርገዉ፣ የጥሪዉን ይዘት እና የጉባኤዉን አጀንዳ የሚወስነዉ ይህንኑ እንዲያደርግ በሕግ እና በማህበሩ የመመስረቻ ፅሑፍ ስልጣን የተሰጠዉ የጉባኤዉ ጠሪ አካል ነዉ፤

1.3. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ቢያንስ በየበጀት ዓመቱ አንድ ጊዜ በዋናው መሥሪያ ቤት ወይም በጥሪ አድራጊዉ አካል በሚወሰን ቦታ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት ውስጥ መካሄድ አለበት፡፡ አስቸኳይም ሆነ ተጨማሪ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በማንኛውም ጊዜ ሊጠራ ይችላል፤

1.4. የጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ የሚደረገዉ ሰፊ ስርጭት ባለዉ ጋዜጣ ወይም በአሌክትሮኒክስ የመገናኛ ብዙሃን ወይም ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን በሚላክ ደብዳቤ ወይም ለዚሁ ዓላማ የማህበሩ ባለአክሲዮን አስቀድሞ በሰጠዉ የኢሜይል አድራሻ ይሆናል፡፡

1.5. ምልዓተ ጉባኤዉ ባለመሟላቱ ምክንያት ለሁለተኛ ጊዜ የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ የሚደረገዉ ወይም ለሁለተኛ እና ለሶስተኛ ጊዜ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ የሚደረገዉ መጀመሪያ በተደረገዉ አኳኋን ነዉ፤

1.6. የየትኛዉም ጉባኤ ጥሪ ከስብሰባዉ ቀን 24 ቀናት አስቀድሞ መሆን ይኖርበታል፤

1.7. መደበኛም ሆነ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ለማድረግ የሚያስፈልገዉን ምልዓተ ጉባኤ እና ውሳኔ ለማሳለፍ የሚያስፈልገዉን የድምፅ ብልጫ እንዲሁም የጉባኤዉ አመራር በንግድ ሕግ አንቀፅ 374፣ 379፣ 380፣ 398 እና 402 መሠረት ይሆናል፡፡

2. የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣን

2.1. በንግድ ሕግ አንቀፅ 394፣ በሌሎች አግባብነት ባላቸዉ ሕጎች እና በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍ ለመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በግልጽ ተለይተው በተሰጡት ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የመስጠት፣

2.2. አግባብ ባለው ሕግ እና በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍ ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በግልጽ ተለይተው ከተሰጡት ጉዳዮች በስተቀር በማንኛዉም ሌሎች የማህበሩ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የመስጠት፣

2.3. የማህበሩን ሀብት አስር በመቶና ከዚያ በላይ የሚሸፍን የጥቅም ግጭት ያለበት ውል እንዲደረግ መፍቀድ፤

2.4. ማህበሩ የራሱን አክሲዮኖች መልሶ እንዲገዛ መፍቀድ፣

2.5. ከፍተኛ ባለአክሲዮኖች ድምፅ ቆጣሪ መሆን ባልፈቀዱ ጊዜ ወይም ጉባኤዉ ሌላ ድምፅ ቆጣሪ መምረጥ በፈለገ ጊዜ ድምፅ ቆጣሪዎችን መምረጥ፤

2.6. በባለአክሲዮኖች ጥያቄ መነሻነት ልዩ መርማሪ መሾም፣

2.7. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን መምረጥ፣

2.8. ማህበሩ ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ብድር እንዲሰጥ ወይም ዋስ እንዲሆን መፍቀድ፣

2.9. ተጨማሪ ወይም አማራጭ የመጠባበቂያ ገንዘብ እንዲኖር መወሰን፣ናቸው፡፡

3. የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣን

3.1. በንግድ ህግ አንቀፅ 400 እና አግባብነት ባላቸዉ ሕጎች መሰረት የማህበሩን መመስረቻ ፅሑፍ ማሻሻል፤ መለወጥ፤

3.2. የማህበሩን ካፒታል ማሳደግ ወይም መቀነስ፤ አክሲዮኖች የሚወጡባቸዉን ዘዴዎች መወሰን፣

3.3. የማኅበሩን የስም ለውጥ ለማከናወን በሚቀርብ የውሳኔ ሃሳብ ላይ ውሳኔ መስጠት፤

3.4. የማህበሩን ዜግነት ስለመለወጥ ወይም ማህበሩ እንዲፈርስ ወይም ወደ ሌላ አይነት የንግድ ማህበር እንዲለወጥ፤ እንዲከፋፈል ወይንም እንዲዋሃድ መወሰን፤

3.5. የማህበሩን ዜግነት ለመለወጥ ውሳኔ ማሳለፍ፤

3.6. ልዩ መብት የሚያስጡ አክሲዮኖች እንዲወጡ መፍቀድ ናቸው፡፡

## አንቀጽ አስራ ሰባት

## የዳይሬክተሮች ቦርድ

1. የአባላት ብዛት፣ ለአባልነት ብቁ የሚደርጉ መስፈርቶች፣ ምርጫ እና የአገልግሎት ዘመን

1.1. የማህበሩ ዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቁጥር ዘጠኝ ነው፤

1.2. ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ብቁ የሚደርጉ መስፈርቶች በህግ እና በተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በሚሰጡ መመሪያዎች መሰረት የሚወሰን ይሆናል፡፡ ሆኖም ከዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል ከሦስት ሁለት እጅ (2/3ኛ) በማህበሩ የዕለት ተዕለት ሥራ አመራር ውስጥ የሥራ አስፈጻሚነት (ኤክስኪዩቲቭ) ሚና የሌላቸው መሆን አለባቸው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በቦርድ አባልነት የሚመረጡ ባለአክሲዮን ያልሆኑ ሰዎች ቁጥርም ከቦርዱ ጠቅላላ አባላት አንድ ሶስተኛ አይበልጥም፤

1.3. ዳይሬክተሮች በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ይመረጣሉ፡፡ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ማህበር የቦርድ አባል ሆኖ ሊሾም ይችላል፡፡ ይህም ሲሆን ተመራጩ በሕግ ሰውነት የተሰጠው ማህበር ለተመረጠባቸው አመታት የሚያገለግል ቋሚ ተወካይ ወዲያውኑ መመደብ አለበት፡፡ ቋሚ ተወካዩ የለቀቀ ከሆነ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት ኃላፊነቱን መወጣት ያልቻለ እንደሆነ ምትክ ተወካይ በተቻለ ፍጥነት መመደብ አለበት፡፡ ቋሚ ተወካዩ በግሉ የማህበሩ ዳይሬክተር አይደለም፡፡ ሆኖም ግን የማህበሩ ዳይሬክተር እንደሆነ በመቁጠር የፍትሐብሔር እና የወንጀል ተጠያቂነትን ጨምሮ ለሁሉም ግዴታዎች ከወከለው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ማህበር ጋር በአንድነት እና በነጠላ ኃላፊ ይሆናል፤

1.4. የዳይሬክተሮች የአገልግሎት ዘመን ሶስት ዓመት ነው፡፡ ሆኖም እንደገና ሊመረጡ ይችላሉ፤

1.5. ለሁለት ተከታታይ የቦርድ የአገልግሎት ዘመናት ያገለገለ ዳይሬክተር የአገልግሎት ዘመኑ ሳይቋረጥ እንደገና ሊመረጥ የሚችለው ለቀጣይነት ሲባል በልዩ ሁኔታ በመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ሲወሰን ለአንድ ተጨማሪ የአገልግሎት ዘመን ብቻ ነው፡፡ ሆኖም ለቀጣይነት ሲባል ለሶስት ተከታታይ የቦርድ የምርጫ ዘመናት የሚመረጡ ዳይሬክተሮች ቁጥር ከጠቅላላው የቦርድ አባላት ቁጥር ከአንድ ሦስተኛ መብለጥ አይችልም፤

1.6. የአገልግሎት ዘመናቸውን የጨረሱ ዳይሬክተሮች እንደገና ሊመረጡ የሚችሉት ሁለት ተከታታይ የቦርድ ምርጫ ዘመናት ካለፈ በኋላ ነው፡፡

## 2. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ተግባር

በንግድ ህግ አንቀጽ 315 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ተግባር እንደሚከተለው ይሆናል፡-

2.1. የማህበሩን ዋና ሥራ አስፈፃሚ መሾምና መሻር፣ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም መወሰን፤

2.2. በንግድ ህጉ ወይም በመመስረቻ ጽሁፍ መሰረት የማህበሩን ጉባኤዎች መጥራት፤

2.3. የማህበሩን አጠቃላይ አመራር፣ ስራና  አስተዳደር መቆጣጠርና መከታተል፣

2.4. የማህበሩን የሥራ አደራጃጀት፣ ሥርዓት፣ መዋቅር፣ የደመወዝ ስኬል፣ የሰራተኞች ጥቅማ-ጥቅምና የውስጥ ፖሊሲዎችን ማጽደቅ፣

2.5. በዋና ሥራ አስፈጻሚ አቅራቢነት ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለዋና ስራ አስፈጻሚ የሆኑ የማህበሩን ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች ቅጥር እና ስንብት ማጽደቅ፤ የሥራ ሁኔታዎችንም መወሰን፤

2.6. የማህበሩን አጠቃላይ ስልት መቀየስ፤ ማጽደቅ፤

2.7. ለባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የማህበሩን ዓመታዊ ሪፖርት ማዘጋጀትና ማቅረብ፣

2.8. በባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የሚወሰኑ ሌሎች ተግባራት ማከናወን፣

2.9. አስፈላጊዉን መረጃ የያዘ የአክሲዮን መዝገብ መደራጀቱን ማረጋገጥ፣

2.10. ከባለአክሲዮኖች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ የመንግስት መ/ቤቶች በስተቀር ሌሎች ሰዎች የባለአክሲዮኖችን መዝገብ  ለማየት እና/ወይም ግልባጭ ለማግኘት እና ለማህበሩ ቅርበት ያላቸዉን ሰዎች መዝገብ ለማየት ሲጠይቁ የሚከፍሉትን ክፍያ መወሰን፣

2.11. በጠቅላላ ጉባኤ ላይ ለመሳተፍ የሚሰጡ የውክልና ስልጣን ቅፅ፣ ይዘት እና ሰነዱ የሚቀመጥበት ቦታና ጊዜ መወሰን፣

2.12. በሕግ ለማህበሩ ባለአክሲዮኖች እንዲሰጡ የተፈቀዱ ሰነዶችና መረጃዎች በተጠየቁ ጊዜ መሰጠታቸውንት ማረጋገጥ፣

2.13. በማህበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ እንዲደረግ የተፈቀደዉን የጥቅም ግጭት ያለበትን ውል በተመለከተ ዝርዝር መረጃ ለሚመለከተዉ አካል ማቅረብና በማህበሩ ድረ-ገፅ ማዉጣት፣

2.14. የቦርድ ንዑስ ኮሚቴዎችን ማቋቋም፣ ሥልጣንና ተግባራቸዉን መወሰን፣

2.15. አንድ ወይም ከአንድ በላይ የቦርድ አባላት አንድን ጉዳይ ወይም የተለያዩ ጉዳዮችን በተመለከተ ማህበሩን እንዲወክሉ፣ ሥራ እንዲሰሩ፣ የውሳኔ ሃሳብ እንዲያቀርቡ የተለየ ኃላፊነት መስጠት፣

2.16. የጎደሉ የቦርድ አባላትን የሚተኩ አባላት መምረጥና የተተኪ አባላት ሹመት እንዲጸድቅ ለተቆጣጣሪው አካልና ለሚቀጥለዉ ጠቅላላ ጉባኤ ማቅረብ፣

2.17. እንደማንኛዉም ደንበኛ የሚደረጉ መደበኛ ግንኙነቶችን ወይም ግብይቶችን ሳይጨምር በማህበሩ እና ከማህበሩ ጋር ቅርበት ባላቸዉ ሰዎች መካከል የሚደረገዉን ውል መፍቀድ፣

2.18. የራሱን የውስጥ የመተዳደሪያ ደንብ ማዉጣትና በደንቡ መሠረት መሥራት፣

2.19. ሕግ በሚፈቅደውና አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ሥልጣኑን በከፊል ለዋናው ሥራ አስፈፃሚ መስጠት/ማስተላለፍ ናቸው፡፡

3. ኃላፊነትና ተጠያቂነት

ዳይሬክተሮች በሕግ፣ በመመሥረቻ ፅሑፍና በባለአክስዮኖች ጉባኤ የተሰጣቸውን ሥልጣን ለመወጣት በጥንቃቄ፣ በቅን ሕሊናና በትጋት የመሥራት ግዴታ ያለባቸዉ ሲሆን ለማህበሩ ጉዳት የሚያመጡ ሥራዎችን እያወቁ ድርጊቱ እንዳይፈፀም ለመከላከል ወይም የጉዳቶችን መጠን ለማቃለል የሚቻላቸውን ያላደረጉ ከሆነ ወይም ግዴታቸውን ያጎደሉ እንደሆነ በአንድነትና በነጠላ ይጠየቃሉ፤ ኃላፊዎችም ይሆናሉ፡፡

4. የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ

4.1. በሌላ ጊዜ ወይም ቦታ እንዲሆን ካልተወሰነ በስተቀር የዳይሬክተሮች ቦርድ በማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት ወይም በርቀት በኤሌትሮኒክስ የስብሰባ ዘዴ ወይም በሌላ አመቺ በሆነ መንገድ በወር ቢያንስ አንድ ጊዜ ይሰበሰባሉ፤

4.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የቦርዱን ስብሰባዎች በቪዲዮ ወይም በሌላ ኤሌክትሮኒክ የመገናኛ ዘዴዎች እንዲደረግ ከወሰኑ የመገናኛ ዘዴው የተሰብሳቢዎቹን ማንነት ለመለየት የሚያስችል እንዲሁም ውጤታማ ተሳትፎን የሚያረጋግጥ መሆን አለበት፡፡ የመገናኛ ዘዴው ቢያንስ የተሳታፊዎችን ድምፅ ሳይቆራረጥ የሚያስተላልፍ እና ተሰብሳቢዎቹ በአንድ ጊዜ መሳተፍ እንዲችሉ የሚፈቅድ መሆን አለበት፤

4.3. ማንኛውንም የቦርድ ስብሰባ ለማካሄድ ከዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ከግማሽ በላይ መገኘት/መሳተፍ አለባቸው፡፡ የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በአብላጫ ድምፅ ነው፡፡ ሆኖም የቦርዱ አባላት ድምፅ እኩል ሲሆን ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፤

4.4. በዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ላይ አንድ የቦርድ አባል በሌላ የቦርድ አባል ሊወከል ይችላል፡፡ ውክልናው በደብዳቤ፤ በፋክስ ወይም በኢሜይል ሊሰጥ ይችላል፡፡ ሆኖም አንድ የቦርድ አባል በአንድ ስብሰባ ላይ ከአንድ በላይ የሆኑ የቦርድ አባላትን ወክሎ መሳተፍ አይችልም፤

4.5. የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ በቃለ-ጉባኤ መያዝ እና በቦርድ አባላት መፈረም አለበት፡፡

5. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ሥልጣንና ኃላፊነት

5.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ወይም ምክትል ሰብሳቢ መሆን የሚችለው ባለአክሲዮን የሆነ ዳይሬክተር ብቻ ነው፤

5.2. በማህበሩ የእለት ተእለት ሥራ አመራር (Executive Management) የሚሳተፍ የቦርድ አባል የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ መሆን አይችልም፤

5.3. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ወይም ምክትል ሰብሳቢ በዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ይመረጣል፤

5.4. የቦርዱ ሰብሳቢ የማህበሩን የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በሰብሳቢነት ይመራል፤

5.5. የቦርዱ ሰብሳቢ በዳይሬክተሮች ቦርድ በውክልና የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

6. **የዳይሬክተሮች የሥራ ዋጋና አበል**

6.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ለሚሰጡት አገልግሎት መጠኑ በመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚወሰን ከጠቅላላ የአስተዳደር ወጪ የሚታሰብ ዓመታዊ የሥራ ዋጋ እና የትራንስፖርት አበል ይከፈላቸዋል፤

6.2. በተጨማሪም የማህበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ከማህበሩ ዓመታዊ የተጣራ ትርፍ ላይ እስከ አስር በመቶ ድረስ ድርሻ ወይም ጉርሻ ለዳይሬክተሮች እንዲሰጥ ሊወስን ይችላል፤ ሆኖም ይህ ክፍያ ለባለአክሲዮኖች ትርፍ እስካልተከፋፈለ ድረስ ለዳይሬክተሮች አይከፈላቸውም፡፡

## አንቀጽ አስራ ስምንት
## ዋና ሥራ አስፈጻሚ

1. የማኅበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በዳይሬክተሮች ቦርድ ይሾማል፤ ተጠሪነቱም ለቦርዱ ነው፤
2. በንግድ ህግ አንቀፅ 338 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማህበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሥልጣን፣ ተግባርና ሃላፊነት እንደሚከተለው ነው፡-

   2.1. በዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ ላይ በመመርኮዝ ማኅበሩ ለተቋቋመበት ዓላማ ግብ መምታት የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል፤

   2.2. የማኅበሩን አጠቃላይ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ያቅዳል፣ ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

   2.3. የማኅበሩን ዓመታዊ በጀት፣ የሥራ ፕሮግራም፤ የሂሣብ ሪፖርት እንዲሁም ሌሎች እንቅስቃሴዎችን ሪፖርትና ሰነድ አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤ ሲጸድቅ ይተገብራል፤

   2.4. በሌሎች የማህበሩ የውስጥ ደንቦች ቅጥራቸዉ በዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲጸድቅ ከተወሰነ የሥራ ኃላፊዎች ውጭ ያሉትን የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ቦርዱ ባጸደቀው

መመሪያ/ፖሊሲ መሰረት ይቀጥራል፤ ያሰናብታል፣ ዕድገት ይሰጣል፣ ያስተዳድራል፣ የሥራ ሁኔታዎችን ይወስናል፤

2.5. በዳይሬክተሮች ቦርድ በተፈቀደው የአሰራር ሥርዓትና የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት ወጪዎችን ያጸድቃል፤

2.6. የማኅበሩን ዓላማ ለማሳደግ ቦርዱ ባጸደቀው ዕቅድ መሰረት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን ያቋቁማል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

2.7. የሥራ መጓተትን የሚያስቀርና ትርፋማነትን የሚጨምር የተቀላጠፈ የውስጥ ቁጥጥር መዋቅርና አሠራር ይዘረጋል፤

2.8. አግባብ ባለው ሕግና ቦርዱ ባወጣቸው መመሪዎች መሠረት በሠራተኞች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤

2.9. በማህበሩ ስም የሚንቀሳቀስ ንብረቶች ሽያጭ፣ ግዥ እና ኪራይ ውል ይፈፅማል፤ ክፍያ ይቀበላል፣ የክፍያ ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፤

2.10. የተሽከርካሪ ጥገና እና ምርመራ ማእከሎችን ያቋቁማል፤ ተዛማጅ ሥራዎችን ያከናውናል፤

2.11. የንብረት አስተዳደርና ጥበቃ ሥራዎችን ያከናውናል፤

2.12. በብድር የተገኘ ገንዘብ በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤ የግንባታና የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በበላይነት ይመራል፤ የማህበሩን የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች ለባንክ ብድር በዋስትና እንዲሰጡ ይፈቅዳል፤ ይኸው እንዲፈጸም ውክልና ይሰጣል፤

2.13. በመመስረቻ ጽሁፍ የተዘረዘሩትን የማህበሩን የንግድ አላማዎች ከግቡ ለማድረስ በማህበሩ ስም ይሰራል፤ ይዋዋላል፤ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ያከራያል፤

2.14. በቅድሚያ የዳይሬክተሮች ቦርድን ፈቃድ በቃለ-ጉባኤ በማረጋገጥ፡-

2.14.1. በማህበሩ ስም ከባንክ ገንዘብ ይበደራል፤ ለዚህ ብድር ክፍያ የማህበሩን የማይንቀሳቀስ ንብረት ያስይዛል፤ የብድርና የመያዣ ውሎችንም ይፈርማል፤

2.14.2. የማህበሩን የማይንቀሳቀስ ንብረት ይሸጣል፤ የሽያጭ ገንዘብ ይቀበላል፤ በማህበሩ ስም የማይንቀሳቀስ ንብረት ይገዛል፣ የግዥ ገንዘብ ይከፍላል፣ ንብረቱንና ሰነዶችን ይረከባል፤ ስመ-ሀብቱ በማህበሩ ስም እንዲዛወር ያደርጋል፤

2.14.3. በማህበሩ ስም በሌሎች የንግድ ማህበራት ወይም ድርጅቶች አክሲዮን በመግዛት በኢንቨስትመንት ይሳተፋል፤ በእነዚህ ተቋማት የባለአክሲዮኖች ስብሰባ ላይ ማህበሩን ወክሎ ይገኛል፤ ማህበሩን ወክሎ ሰነዶችን ይፈርማል፤ ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፤ ገቢ ይሰበስባል፤ አስፈላጊነቱን ሲያምንበትም ለማህበሩ ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞች ውክልና ይሰጣል፤

2.15. የማህበሩን አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ በመቃወም ከማህበሩ ለመዉጣት የሚፈልጉ ባለአክሲዮኖችን ጥያቄ ይቀበላል፤ በህግ መሰረት ውሳኔ ይሰጣል፤

2.16. በማንኛዉም ፍ/ቤት ማህበሩ የክርክር ተካፋይ ሲሆን ማህበሩን በመወከል አስፈላጊዉን ይፈፅማል፤ ማህበሩን የሚመለከት ጉዳይን በዕርቅ፣ በግልግል ወይም በስምምነት ለመጨረስ ይችላል፤ እንደአስፈላጊነቱ የሕግ ባለሙያ ወይም ጠበቃ ይወክላል፤

2.17. ማህበሩ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር በሚያደርጋቸው የሥራ እንቅስቃሴዎች ከሦስተኛ ወገኖች፤ በህዝባዊ ተቋማት እና የግል ድርጅቶች፤ ባንኮች፤ ወይም ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ፊት ማህበሩን ወክሎ ይገኛል፤

2.18. በማህበሩ ስም የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፤ ያንቀሳቅሳል፤ የገንዘብ መክፈያ ሰነዶች፤ ቼክ፤ የሀዋላ ወረቀቶች፤ የተስፋ ሰነዶች እና ሌሎች ተላላፊ የገንዘብ ሰነዶችን ይፈርማል፤ ይቀበላል፤ ያስተላልፋል፤ ክፍያዎችን ይቀበላል፤ ይፈጽማል፤

2.19. በሕግም ሆነ በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባር እንደአስፈላጊነቱ በሙሉም ሆነ በከፊል ለሌላ ሰዉ በሥራ ዝርዝር ወይም በውክልና ያስተላልፋል።

2.20. ከላይ ከተጠቀሱት ተግባሮች ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን ሌሎች ጉዳዮችና ሥራዎች ያከናውናል፤

## አንቀፅ አስራ ዘጠኝ

## የማህበሩ ፀሐፊ

1. የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እና የዳይሬክተሮች ቦርድ ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል፤
2. ከጉባኤዉ ሰብሳቢ እና ከዋና ሥራ አስፈጻሚ ጋር በመመካከር የጉባኤዎቹን አጀንዳ ያዘጋጃል፤ የጉባኤ ጥሪ እንዲተላለፍ ያደርጋል፤ ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፤ በዳይሬክተሮች እንዲፈረም ያደረጋል፤ በብሔራዊ ባንክ እና በሰነዶች ማረጋገጫ ጽሕፈት ቤት መፅደቁን በማረጋገጥ፣ ቃለ-ጉባኤዎችን በአግባቡ እና በጥንቃቄ ያስቀምጣል፤
3. የዳይሬክተሮች ቦርድ እና የቦርድ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ስብሰባዎች ያዘጋጃል፣ ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፤ በአግባቡ ያስቀምጣል፤
4. በዳይሬክተሮች ቦርድ እና በኤክሲክዩቲቭ ማኔጅመንት መካከል እንደድልድይ ሆኖ ያገላግላል፤ በሁለቱ መካከል የሚደረገዉን ግንኙነት ያሳልጣል፤
5. በቦርድ ወይም በዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል፤
6. የጠቅላላ ጉባኤ የተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ ላይ በስብሰባዉ መጀመሪያ ላይ በአካል ወይም በወኪል በተገኙ ባለአክሲዮኖች መፈረማቸዉን ያረጋግጣል፤

7. በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 የተመለከቱትን በመተላለፍ በማህበሩ፣ በባለአክስዮኖች ወይም በሦስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊ ይሆናል፤
8. ሌሎች በሕግ የተሰጡትን ኃላፊነቶች ይፈፅማል፤ ያስፈፅማል፡፡

## አንቀጽ ሃያ

## የማህበሩ ኦዲተር

1. በኢትዮጵያ የንግድ ህግ አንቀፅ 348 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማህበሩ ኦዲተር ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩ ሃላፊነቶች አለበት፤
   1.1. የማኅበሩን መዛግብትና ሰነዶችን መመርመር፣
   1.2. የማኅበሩን ንብረት፣ የሂሣብ ሚዛንና ትርፍና ኪሣራን የሚያሳዩትን መዛግብት ትክክለኛነት ማረጋገጥ፣
   1.3. የዳይሬክተሮች ቦርድ የሰጠው ሪፖርት የማኅበሩን ትክክለኛ ገጽታ የሚያሳይ መሆኑን ማረጋገጥ፣
   1.4. ሥራውን ለማከናወን አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምንበትን መዝገብ፣ ሰነድ፣ ቃለ -ጉባዔ ሌሎች መረጃዎችን ባሉበት ማየትና መመርመር፣
   1.5. በመደበኛ እና በማናቸውም የባለአክሲዮኖች ጉባዔ ላይ መገኘት፣
   1.6. ሁሉም የቦርድ አባላት ሥራቸዉን በተዉ ጊዜ ተተኪ የቦርድ አባላት እንዲሾሙ ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት እና እስከ ጠቅላላ ጉባኤ ድረስ ማህበሩን ማስተዳደር፤
   1.7. ሌሎች በሕግ የተደነገጉ ግዴታዎችን መፈጸም፡፡

## አንቀጽ ሃያ አንድ

## የሂሳብ አያየዝ ሥርአት

ማህበሩ በሕግና በንግድ አሠራር መሠረት ተቀባይነት ያለው የሂሳብ አያየዝ ሥርዓት ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ ሃያ ሁለት

## የማህበሩ ዓመታዊ ሪፖርት

ማህበሩ ዓመታዊ የፋይናንስ ሪፖርቱንና ሌሎች በህግ የሚጠበቁ ሪፖርቶችን ያዘጋጃል፡፡

## አንቀጽ ሃያ ሦስት

## የማህበሩ የበጀት ዓመት

የማህበሩ የበጀት ዓመት እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር ከጁላይ 1 እስከ የሚቀጥለው ዓመት ጁን 30 ቀን ነው፡፡

## አንቀጽ ሃያ አራት

## ስለማኅበሩ መፍረስና ሂሣብ ማጣራት

ማኅበሩ በሕግ ወይም በባለአክሲዮኖች ውሳኔ ሊፈርስ ይችላል። ሂሳብ ማጣራቱና አፈጻጸሙም በንግድ ህግ ድንጋጌዎች መሰረት ይሆናል።

## አንቀጽ ሃያ አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

1. ማህበሩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው፤
2. በዚህ መመስረቻ ጽሑፍ በግልጽ ያልተካተቱ ጉዳዮች በንግድ ሕጉ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት ይወሰናሉ፤
3. ይህ የተሻሻለ መመስረቻ ጽሁፍ በማናቸውም ጊዜ በባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ ይችላል፤
4. ይህ የተሻሻለው የመመስረቻ ጽሑፍ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ጸድቆ ስራ ላይ እስከሚውል ድረስ ነባሩ መመስረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ በስራ ላይ የሚቆዩ ሲሆን በነዚህ መሰረት የተከናወኑ ተግባሮች ሁሉ ህጋዊ ውጤታቸው የሚቀጥል ይሆናል።
5. የተሻሻለው የማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው ፀድቆ ሥልጣን ላለው የመንግሥት አካል ቀርቦ ከፀደቀና ከተመዘገበ በኋላ ተፈጻሚ ይሆናል።

የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስምና ፊርማ

| ተራ ቁ. | ሙሉ ስም | ኃላፊነት | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ኃይሉ አለሙ ማሙዬ | ሰብሳቢ | |
| 2 | አቶ አባተ ግዳፌ ከተማ | አባል | |
| 3 | አቶ ሞገስ አባይነህ በቀለ | አባል | |
| 4 | ዶ/ር ኢያሱ መኮንን ጀምበር | አባል | |
| 5 | አቶ በሻዳ ገመቹ ጉደታ | አባል | |
| 6 | ኢንጂነር ራሔል ኮሬ ጉራች | አባል | |
| 7 | ኢንጂነር ወልዳይ በርሔ ደሳለኝ | አባል | |
| 8 | አቶ በላይነህ ይልማ ታረቀኝ | አባል | |
| 9 | ዶ/ር ማሪያማዊት ዮናታን ይስሀቅ | አባል | |